# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።
# Ethiopia: The Kingdom of God Services

---

## <u>ለኢትዮጵያ መጸለይ እና መጾም ማለት፡</u>
## <u>በቅድሚያ፡ ራስን፡ በንስሐ፡</u>
## <u>ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማብቃት ማለት ነው።</u>

እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፥ የኢትዮጵያ ወዳጆች የኾኑ ወገኖች ኹሉ ጭምር፡ “ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!” “ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!” የሚለውን፡ ሕያው የአምላክ ቃል በመከተል፡ በተለይ፡ ስለኢትዮጵያ ደኅንነትና ሰላም፥ በአጠቃላይም፡ ስለመላው ዓለም፡ በያለንበት፡ የሦስት ቀኖች ጾምና ጸሎት እናደርግ ዘንድ፡ “ሰላም ለኢትዮጵያ” ኅዋ ሰሌዳ (Web Site) ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል።

በዚህ ማሳሰቢያ መነሻነት፡ “ሰላም ለኢትዮጵያ”፡ በተለይ፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት ካቀረበው ጥያቄ፡ ባገኘው መልስ መሠረት፡ ይኸው ጾምና ጸሎት፡ ከጳጉሜ ፩ እስከ ፫፥ ቢቻልም፡ እስከ ፯ ቀን፥ ፲፱፻፺፱ ዓ. ም. ድረስ ተራዝሞ እንዲፈጸም፡ በስምምነት ተወስኗል። ይኸው የኅዋ ሰሌዳ፡ ይህን ውሳኔ፡ በተግባር ላይ ለማዋል፡ መነሻ ያደረጋቸው መሠረታውያን የኾኑ፡ በቂ ምክንያቶች፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ ባጭር ተገልጸዋል።

፩ኛ. ክህነታዊ ሥልጣንንና ኃላፊነትን የሚጠይቀው፥ በሥርዓትም ሊፈጸም የሚገባው፡ ይኸው አሳብና ውሳኔ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ተጠሪ በኾኑለት፡ በ“ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት” ዋቢነት ተካኺዶ ሊከናወን እንዲችል፡ ፈቃዳቸው በመገኘቱ ነው፤

፪ኛ. በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የዓመቱ፡ “፲፫ኛ (አሥራ ሦስተኛ) እና የመጨረሻዋ ወር” የምትባለው ጳጉሜ፡ ቀድሞም ቢኾን፡ “አዲሱን ዓመት፡ በታደሰ የነፍስ ንቃት፥ የሥጋ ንጽሕናና የመንፈስ ብቅዓት ለመቀበል፡ በሃይማኖታዊ ሥርዓት፡ ቤትንና ቍሳቁሱን ማጥዳት፥ ልብስን ማጠብና ገላን፡ በጠበል ውኃ ማንጻት ብቻ ሳይኾን፡ በኃጢኣት ስሜትና በክፋት ድርጊት ያደፈውን የሰውነትን ውሳጣዊ ኹለንተናም፡ በንስሓ ጭምር ማጥራትና በቅዱስ ቍርባን ማጽደቅ ይገባል!” በሚል እምነት፡ በተለይ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በጾምና በጸሎት የሚያሳልፏት ኾና ስለኖረች ነው።

፫ኛ. ለጸሙና ለጸሎቱ የተወሰነው፡ ይኸው ጊዜ፡ ኢትዮጵያ፡ በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት ኾና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሠ ነገሥትነት፥ በድንግል ማርያም እናት አገርነትና ንግሥትነት፡ በፍጹም ነጻነት የኖረችበትን፡ የ፯ሺ ፭፻ (የሰባት ሺ አምስት መቶ) ዓመታት ህልውናዋን መታሰቢያ ከምታከብርበት፡ ከታላቁ በዓሏ ዋዜማ ላይ መዋሉ የተለየ አጋጣሚ በመኾኑ ነው።

ኢትዮጵያ፡ ልጆቿን ይዛ ያሳለፈችው፡ ይህ ያልተቋረጠው የነፃነት ህልውናዋና ብሔራዊ ልዕልናዋ፡ ያለውልውል፡ በበለጠ የሚያረጋግጠው፡ አንድ ጸንቶ የኖረ እውነት አለ፤ ይኸውም፡ ይህች ቅድስት እናት አገር፡ በመለኮታዊው መንግሥት ሥር እየተመራችና እየተዳደረች፥ ልጆቿ ሲያጠፉ፡ በአኹኑ ጊዜ የሚሠቃዩበትን ፈተናና መከራ በመሰለ ፍርድ እየተቀጡ፥ በንስሓ ሲመለሱ ደግሞ፡ አምላካዊ ምሕረትን እያገኙ፡ እርሷ፡ ከነልጆቿ፡ ምንጊዜም፡ በቅዱሱ ኪዳን ተጠብቃ የኖረችና ያለች፥ ወደፊትም የምትኖር መኾኗ ነው።

“ለኢትዮጵያ መጸለይ እና መጾም” ማለት ደግሞ፡ በቅድሚያ፡ ራስን፡ በንስሓ፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማብቃት ማለት ነው። ይህም፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና አምልኮ፡ ታማኝ ኾኖ በመገኘት፥ ምግባሩንና ሥርዓቱንም፡ በትክክል ተከትሎ በመፈጸም፡ ወደፊት ሊመጣ ባለው፡ በዘለዓለማዊው ዓለም ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ፡ እዚሁ፡ አኹን በምንገኝበት፡ በዚህ ዓለም ጭምር፡ ፍጽምትና ሉዓላዊት የኾነችውን መልካሟን ሕይወት፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ መኖር ነው።

ይህን ጾምና ጸሎት፡ በቅርቡ እንድናደርግ፡ እጅግ አስፈላጊ የኾነበት ምክንያት፥ በምን መልክ ልንፈጽመው እንደሚገባም፥ ሥርዓቱን ጭምር፡ በዝርዝር አብራርተው ያሳውቁን ዘንድ የተዘጋጁት ጽሑፎች፡ ይኸው፡ ከዚህ መልእክት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል። ስለዚህ፡ የተወሰኑትን የጾምና የጸሎት ቀኖች፡ በእውነትና በትክክለኛው አምልኮ ፈጽመናቸው፡ ጣፋጩን ፍሬ ለመሰብሰብ ይቻለን ዘንድ፡ እነዚህን ጽሑፎች፡ ከአኹኗ ዕለት ጀምረን በጥንቃቄና በማስተዋል፥ በጽሙናና በተመስጦ እንመልከታቸው!

መሓሪውና ኃያሉ እግዚአብሔር፡ ፈቃዱ ነውና፡ በእኛ በኩል፡ ኹላችንም፡ ለዚያች፡ ለጳጉሜ የጾምና የጸሎት ቀጠሮአችን፡ እየራሳችንን፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ አብቅተን ለመገኘት፡ የቆረጥንና የተዘጋጀን እንኹን!

የጾሙንና የጸሎቱን መልእክትና ሥርዓት፡ በሙሉ ለመመልከት፡ እነዚህን፡ የመግቢያ ቁልፎች፡ እያንዳንዳቸውን በመጠቄም መክፈት ያስፈልጋል።

የጾመ ኢትዮጵያ መልእክት (ምልክቱ)
የጾመ ኢትዮጵያ ሥርዓት "